PANORAMA # XVLII

**የትዝብት አድማስ**

**መስከረም 9 ቀን 2001 ዓም**

**<u>እንደ ገና ዳቦ በሁለት እሳት መካከል መቃጠል፡፡</u>**

**ችግሩን በማወቅ ይሁን፥ በአለማወቅ፥ ጠላትን በመለየት ይሁን በአለመለየት፥ ወዳጅን በማቅረብ ይሁን በማራቅ፣ ብዙ ጥቃት እንደደረሰብን ከእኛው ከራሳችን የበለጠ ጉዳቱን የሚያውቅልን የለም፡፡ በሠላሳ ስድስት ዓመታት ውስጥ ሦስት ሥርዓቶች ተፈራርቀውብናል፡፡ የሦስቱም ሥርዓት መስራቾችና አራማጆች ተቀያይረዋል፡፡ ዕልፍ ሲሉት ዕልፍ ይገኛል በሚለው ባኅላዊ አባባል የተዘናጋን ይመስል፣ ከአለፈው የሚመጣው ይሻል ይሆናል በማለት የቀቢፀ- ተስፋ ሰለባ በመሆን ብዙ ተጠቅተናል፡፡ አዲስ የመጣውን ማንነቱን በሚገባ ሳናውቅ፣ እስኪ ደግሞ ይህኛውን እንየው በማለት ብዙ ተጎድተናል፡፡ የሚመጣውን ዕምነቱን እያጎደለ ከድቶናል፡፡ ቁጭ ብለን የሰቀልነውን ቆመን ማውረድ እየተሳነን ተቸግረናል፡፡ ከባኅል ጋር በተየያዘ ዕምነት መንስዔ ዘመን ሲለወጥ፥ መስከረም ሲጠባ፥ ህዳር ሲታጠን፥ የግንቦት ልደታ ሲመጣ ያልፍልን ይሆናል በማለት፥ የጨነቀው ሙቅ አነቀው እየተባባልን ተዘባብተናል፡፡ የሄደው ያደንዝዝ የሚመጣው ያፋዝዝ ሆኖብን ተቸግረናል፡፡**

**የታሪክ ባለፀግነታችንንማ ማንስ መቸ ይነጥቀናል፡፡ የበርካታ ሺ ዘመን ያልተቆራረረጠ ነፃነት፥ የታላላቅ ሃይማኖቶች መዲናነታችን የአድዋ ዓይነት ድሎች ከባህረ-መዝገባችንን ማን ይፍቅብናል? ብቻ በዘመናት የተፈፀሙ አኩሪ ታሪኮች አሁን ከገባንበት ማጥ ሊያድኑን ባለመቻላቸው ተቸገርን እንጅ፡፡ የዘመናችን ታሪክ ሰሪዎችን እንዳናወጣ፥ ጀግኖች እንዳንፈጥር፥ መሲህ እንዳናበቅል፥ እስከ ሰባት ቤታችን ድረስ የተረገምን ይመስል ዛሬ በዳፍንት ፅልመት ውስጥ የገባን መስለናል፡፡ ተስማምተን ቁም ነገር መሥራቱ ይቅርና ላለመስማማት እንኳን መስማማት አቅቶናል፡፡የሃይማኖት አባቶች፥የሀገር ሽማግሌዎች፥አረጋውያን ባልቴቶች ንኳን ሳይቀሩ አንገት መድፋቱን፥ ድምፅ ማጥፋቱን መርጠውታል፡፡ደራሲያን ምሁራንና የኪነት ሰዎች ሳይቀሩ "ዝም አይነቅዝም" የሚለውን ይትበኃል በሥራ ለማዋል የወሰኑ ይመስላሉ፡፡ እንደ ዲዮጋን በጠራራ ፀሀይ ፋኖስ አብርቶ ሰው የሚፈልግ ሰው ዛሬ የሚያስፈልጋት ኢትዮጵያ ነች፡፡ ግን እስቲ ስው ልፈልግ ብሎ የተነሳውን ሰው እንዳናጠፋው እንጅ! ዛሬ ጋኖቹ ተሰብረው ምንቸቶች ጋን ሆነዋል፡፡ ዛፎቹ ተቆራርጠው ቁጥቋጦች ዛፎች ሆነዋል፡፡ የህይወታችን ሁለንተናዊ ሂደት የፈና-ጅራ፥ ለሰሚው ግራ ሆኖብናል ፡፡ ከየት ተነስተን ወዴት እንደምንሄድ አቅጣጫው ተሰውሮብናል፡፡ ይህ ሁሉ ሆኖ ግን ነገ ብሩህ ቀን ይሆናል የሚል ተስፋችንን በትግል ለማጀብና እውን ለማድረግ ከመጣር መራቅ**

እንደሌለብንም እናወቀዋለን፡፡ ከዚህም በላይ “ ከሽ ጨለምተኛ አንድ ቆራጥ አርበኛ” እንደሚያስከነዳም” እንረዳለን፡፡

የሰፈነውን መፋዘዝ ቀቢፀ ተስፋ ስንቃኝ በመሠረቱ ከላንበት ጨለማ ወጥተን እንድንገኝ በጨለማ መዘፈቀቻንን ማወቅ ስላለብን እንጂ ነጋ ጠባ ሙሾ ለማሰማትና ራሳችንን በሳማ ለመግረፍ፤ተስፋችንን ለመስበር አይደለም፡፡ መነገር ያለበት ግን መነገር ይገበዋል፡፡ “ሆድ ይፈጀው፥ ተው ቻለው ሆዴ፥ ክፉ ቀን ያልፋል” እያልን ቆራጥ ርምጃ ከመውሰድ አንቆጠብም፡፡ ክፉ ቀን ያልፋል ቢባልምና እስኪያልፍ የሚያለፋ መሆኑን ብንገነዘብም፥ አልፌውን አልፍተን በአቸናፊነት እንደምንወጣ ደግሞ አንጠራጠርም፡፡ “ ሞልቶ ሲገነፍል ሰው ችግሩ በዝቶ፥ ከልጅ የበለጠ ምን ዘመድ ተገኝቶ?” የሚባለውን የጥንት ዜጎች የብሶት እንጉርጉሮ ዘንግተን፥ ለሀገራቸው ዕድገት፥ ለሕዝባቸው ነፃነትና ዴሞክራሲያዊ መብት የተሰውልንን ልጆቻችንን፥ እናብጠልጥላቸዋለን፡፡ ክቡር አፅማቸው እንኳ በፀጥታ እንዳያርፍ፥ እንኮንነዋለን፡፡ በባህላችን እማ ቢሆን ኖሮ፥ “ የፊት ወዳጅህን ቅበረው በሻሽ፥ የኋለኛው እንደይሸሽ” መባል ነበረበት፡፡ ሰማዕታት ጀግኖችን ያላከበረ ኅብረተሰብ ደግሞ አዳዲስ ጀግኖች ያወጣል ተብሎ አይጠበቅም፡፡ ባኩሪው ታሪካችንማ፥ ጀግና ብቻ ሳይሆን የጀግና ሚስትና ባል፤ ልጆች ሁሉ ይከበራሉ፥ ይወደሳሉ፥ ይረዳሉ፡፡ የዘመናችን ሰማዕታት ግን እንኳን ልጆቻቸው፥ እነርሱ ራሳቸውም ቢሆን የት እንደወደቁ? ምን እንዳገኛቸው? ዘወር ብሎ የሚያያቸው ብዙ አይደለም፡፡ “ ኢትዮጵያ በዕውነት ሰው ይውጣብሽ፥ በድየሽ ከሆነ! ለአንች ለሀገሪ ደሜን እንዳላፈሰስኩልሽ፥ አጥንቴን እንዳልከሰከስኩልሽ ሁሉ፥ ልጆቸን በርሀብ ትገያቸዋለሽ፡፡ ባለቤቴም የትም ወድቃለች፡፡” በማለት ሰማዕታት ጀግኖቿ አቤቱታቸውን እንደሚያሰሙ ይህ የአሁኑ ትውልድ ይገነዘበው አይገነዘበው ባናውቅም፥ በአንድ ሀቅ ግን ሁላችንም ልንስማማ እንችል ይመስለናል፡፡ ይኸውም፥ ትላንት የሀገራቸውን ዳር ድንበር ለማስከበር በየጠረፉ፥ በየበረሃውና በየሸንተረሩ ሲዋደቁ የነበሩ የቀድሞው የመከላካያ ሠራዊት አባሎች፥ ዛሬ የሚቀምሱት የሚልሱት አጥተው በየጎዳናዎቹ ምፅዋዕት እየለመኑ መገኘታቸው  ነው ይህ ደግሞ ብሔራዊ ኩራት ሳይሆን፥ ለዛሬው ትውልድ ሀፍረትና አሰቃቂ ዕውነታ ነው፡፡ የሙሶሊንን የጣሊያን ወራሪ ጦር የተዋጉት አርበኞች ልጆችም ያቋጠራቸው እንዳልነበረ በታሪክ የተመዘገበ ብሔራዊ ሰቆቃእንደነበር እናስታውሳለን፡፡ ኮሪያና ኮንጎ የዘመቱትም የተሻለ ዕድል አለጋጣማቸውም፡፡ ለፍታ ያሳደጋችውና ያስተማረቻቸው ልጆቿ በትግል ተሰልፈው በሽብርለተቀጠፉባት ወላጅ አለሁልሽ ያላት  የለም አልተሰማም፡፡  አላያንም፡፡

ኢትዮጵያ ሀገራችን ለጀግኖቿ የማታስብ ውለታ ቢስ ሀገር እንድትባል የሚፈልግ ንፁኅ ኅሊና ያለው ዜጋ አለ ብለን ለመናገር እንቸገራለን፡፡ ምናልባት በአሁኑ ስዓት ኢትዮጵያ እንደ ሀገር ተወቃሽ ልትሆን አይገባትም የሚል አመለካከት እንደሚኖር እንገነዘባለን፡፡ ትክክልም አመለካከት ነው፡፡ ያም ሆኖ፥ ዞሮ ዞሮ ኃላፊነቱን ሊሸከም የሚችለው፥ሀገሪቱን አስተዳድራለሁ የሚለው ቡድን መሆኑ ግን አከራካሪ አይደለም፡፡ ሠራዊቱን በትኖ፥

EthioLion.com

ሀገሪቱንም ለዘረኞች አስረክቦ የፈረጠጠውን ቡድን ጉዳይ ዛሬ እያነሱ ቢጥሉት፥ በፈርስ ላይ ከማኳኳር በስተቀር፥አሁን ከገባንበት ማጥ እንዴት እንውጣ ከሚለው አንፃር ሲታይ፥ ጭራሽ የሚያመጣው ፋይዳ ይኖራል ብለን አንገምትም፡፡ ከዚህም በቀር፥ የዛሬው ትውልድ፥ የሞተ ፈረስ ጋላቢ፥ የደረቀ ወንዝ ተሻጋሪ ይመስል በበድን ላይ ጊዜውን ማጥፋት አይቻለውም፡፡ ዛሬ ሊሆን የሚገባው ሀገሪቱን ከጥፋት ለማዳን፥ ትኩረቱ፥ የቅድሚያ  ቅደም ተከተሉ ምን መሆን አለበት ነው፡፡ ተደጋግሞ እንደሚታ መንበት ትኩረቱና የቅድሚያ አጀንዳው ወያኔን ማስወገድ መሆኑ ለማነኛውም ሀገር ወዳድ ዜጋ ግልፅ ነው፡፡ ይህ ከሆነ ዘንዳ ጥያቄው ወያኔ እንዴት ይወገድ? ማን ያስወግደው? እረ ለመሆኑ ወያኔን መጣል የማይቻልበት ምን ምክንያትስ ይኖራል? ከነገረ ቀደም፥ በአሁኑ ስዓት ወያኔ የኅብረተሰብ ድጋፍ አለኝ የሚለው ክፍል አለ? የወያኔ ጥንካሬው እምኑ ላይ ነው? የዓለም አቀፍ ፖሊቲካ ለወያኔ ያለው ድጋፍ/ አመለካከት የቱን ያህል ነው? የትግሉ ስልትስ ምን መሆን አለበት? ወያኔን ለመጣል በሚደረገው ትግል የኅብረተሰቡ ድርሻ ምንድን ነው?  የጥያቄዎቹን ዝርዝር ማርዘሙ  የማይጠቅም ቢሆንም፥ ዋና ዋና የሆኑት ግን በጊዜ መልስ ማግኘት አለባቸው፡፡ ወያኔን እቃወማለሁ ያለ ድርጅት ካለ ያመረቃ ትግል ማሳየት ሊኖርበት የግድ ይላል፡፡ ትግል ደግሞ መሥዋዕትን ይጠይቃል፡፡ ምክንያቱም ነፃነት በሌላ  መንግድ አይገኝምና ነው፡፡ድርጅት ለትግል፥ ትግል ለመስዋዕት፥ መስዋዕት ለስርየት፥ ስርየት ለነፃነት፥ የአንዱ መፈጠር ሌለውን እየወለደና አንዱ ከሌላው ፥ እየተቀባበለ እስካልሄደ ድረስ፥ ጉዟችን ሁሉ እንደ ግመል ሽንት ወደኋላ ከመሄድ አይድንም፡፡ ወያኔ የዚህ ሂደትና ድምር ውጤት ምን ሊያስከከትልበት እንደሚችል ደህና አድርጎ የሚረዳ መሰሪ ቡድን መሆኑን ሁሉም ዜጋ ሊረዳው ይገባል፡፡ ከኢትዮጵያ ሕዝብ አመፅ ለመከላከል ሲል ዛሬ ወያኔ በአምሳለ-ስታሊን የተዋቀረ የስለላ ድርጅት አለው፡ ባጀቱም አያሌ ሚሊዮን ብር እንደሆነ ይታመናል፡፡ በታወቁ የውጭ ሀገር የስለላ ድርጅቶች የሰለጠነ የአፋኝና የገዳይ ሰራዊት በማዕከል የተዋቀረ ግብረ ኃይል አለው፡፡  ከነፍስ-ወከፍ የስላዮች ስምሪት አንስቶ ቴሌፎን መጥለፍ፥ የግል ደብዳቤዎችን መቅደድን አካትቶ፥በልዩ ልዩ የኅብረተሰብ ውስጥ የተሰገሰጉትን ጆሮ ጠቢዎችን ያጠቃልላል፡፡ በምርመራ ጊዜ ለማሰቃያ የሚጠቀምባቸውን ዘመናዊ የአካል ማሰቃያ ( ግብረ-ስየል- ቶርቸር) መሳሪያዎች ኤም አይ ሲክስ ከተሰኘው የእንግሊዞች የስለላ ድርጅት ከአሜሪካና ከአንድ ሌላ የመካከለኛው ምሥራቅ ካለ የስለላ ድርጅት ይሰጠዋል፡፡ የወያኔ መርማሪዎቹንና አሰቃዮችንም በዘመናዊ ዘዴ የሚያሰለጡናቸው እነዚሁ የውጭ የስለላ ድርጅቶች ናቸው፡፡ ከጥቂት ዓመታት በፊት አሰፋ ማሩን በጠራራ ፀሀይ በግፍ ወያኔዎች የገደሉት ከእንግሊዝ በተሰጣቸው መኪና ተከታትለው እንደነበር እናስታውሳለን፡፡ ቀደም ባሉት ወቅቶች ጀምሮ፥የወያኔ ብሔረ-ሰብ ታማኝ አባላት ወደ አሜሪካ እየተላኩ፥ ሉዚያና በሚባለው ስቴትስ ወይም

ጠቅላይ ግዛት ባተንሩኧ በሚባለው ከተማ እያፈኑ መግደል ሥልጠና ተሰጥቷቸው ተመልሰዋል። ይህ ሂደት በየጊዜው ወደ ተለያዩ የስለላ ተቋማት እየሄዱ የሚሰለጥኑት የወያኔ ሰላዮች በርካታ ናቸው። የቋንቋ መሀይሞች ስለነበሩ፥ የመማሪያ መጽሀፉን የተረጎመው በአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት አማካኝነት በወቅቱ ወያኔን አትንኩብኝ እያለ ያዙኝ ልቀቁኝ ሲል የነበር የትግራይ ተወላጅ ነው። ሠልጣኞቹን በሚማሩበት በክፍል ውስጥ ሲያስተረጉምላቸው የነበረው፥ ደግሞ ዛሬ የጋዜጦችን ማህበር ለማፍረስ አዲስ አበባ ተመልሶ የሚራወጥ የወያኔ ግብረ- በላ እንደነበር በውቅቱ ተደርሶበት ተጋልጧል። ፀጥታን እናስከብራለን በሚል ሽፋን፥ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ተሳፋሪዎችን በማስፈራራትና የሥነ ልቦና ጭንቀት በማሳደር ተግባር የተሰማሩትን የአፋኝቡድኖች ያሠለጠናቸው ሞሳድ የተባለው የእሥራኤል የስለላ ድርጅት መሆኑ የአደባባይ ምሥጢር ሆኗል። እነኝህ አፋኞች የሚታጠቁትም፥ ኢጣሊያ- ሠራሽ የሆነበሬታ ቁጥር 7 ግማሽ አዉቶማቲክ ሽጉጥ እንደሆነ ማንም ተሳፋሪ ያውቀዋል። ዛሬ ይህች ባለቤት ያጣች ሀገራችን የምትገዛው ብሄራዊ ስሜት ጭራሽ በደማቸው ያልፈጠረላቸው አጥፊ ቡድኖች በመሆኗ፥ ለማነኛውም የባዕዳን የስለላ ድርጅት ተጋልጣለች። በመሆኑም የሀገሪቱን ውስጠ-ምሥጢር ዘክዝከው ለመውሰድ መልካም አጋጣሚ ሆኖላቸዋል። በኢትዮጵያ ውስጠ - ምሥጢር ጓዳ በመግባት እንደልባቸው እንዲዋኙበት ከተፈቀደላቸው የውጭ የስለላ ድርጅቶች መካከል:- የአሜሪካው ሲ አይ ኤ፥ የሩሲያው ቀድሞ ኬ ጅ ቢ ይባል የነበረው፥ የእንግሊዙ ኤም አይ ፋይቭ፥ የእሥራኤሉ ሞሳድ፥ እና የግብፁ ሙኻባራት ይገኙባቸዋል። የወያኔን የውስጥ መሰሪነት፥ ከሀዲነት፥ ተግባር፥ ምንነትና አካሄድ እየተከታተሉ ለሕዝብ ማሳወቅ ከትግላችን አንዱ ዘርፍ በመሆኑ ይህንን ከማድረግ አንቆጠብም። መላው ሕዝባችንም፥ ነቅቶ በመጠበቅ ሀገራችን ጠፍታ እንዳትጠፋ የተቻለውን ሁሉ እንዲከላከል እናሳስባለን።

ዛሬ ሀገራችን እንደ ገና ዳቦ ከላይ በፍህም ከታች በነዲድ እሳት ሆና ትቃጠላለች፥ ትነዳለች፥ ትንገበጋባለች፥ ታርራለች፥ ትኮማተራለች። በላይ የወያኔ የዘር ከፋፋይ ፖሊቲካ ፍህም ያቃጥላታል። ከታች የተገንጣዮች እሳት ይለበልባታል። በጎንና በጎኗ ደግሞ የሀገራችን የቅርብና የሩቅ ጠላቶች ቀስፈው ይዘዋታል።ይህችን ብርቱ ምጥ የያዛትን ሀገር፥ ከስቃይዋ የምናገላግላት እኛው ልጆቿ መሆናችንን ከረሳን፥ ከታሪክና ከሚመጣው ትውልድ ወቀሳና ፍርድ ነፃ እንደማንወጣ ማወቅ ይኖርብናል። ሀገራችንን ለባዕድ አጋልጦ ሰጥቶ የሚያዋርዳትን የወያኔን ከሀዲ ቡድን በትግላችን አስወግደን ሀገራችንን እናድን። በሁለንተናዊ አቅጣጫና ረድፍ ይህንን ከሃዲ ሀገር አጥፊ ቡድን አስወግዶ ሀገራችንን ከጥፋት ለማዳን ቆርጠን እንድንነሳ ጥሪው ተላልፏል።

EthioLion.Com